የኢነርጂ ፖሊሲ ግምገማ

# ኢትዮጵያ 2026

**አበይት ሃሳቦች**

# INTERNATIONAL ENERGY AGENCY

The IEA examines the full spectrum of energy issues including oil, gas and coal supply and demand, renewable energy technologies, electricity markets, energy efficiency, access to energy, demand side management and much more. Through its work, the IEA advocates policies that will enhance the reliability, affordability and sustainability of energy in its 32 Member countries, 14 Association countries and beyond.

**IEA Member countries:**

Australia
Austria
Belgium
Canada
Czech Republic
Denmark
Estonia
Finland
France
Germany
Greece
Hungary
Ireland
Italy
Japan
Korea
Latvia
Lithuania
Luxembourg
Mexico
Netherlands
New Zealand
Norway
Poland
Portugal
Slovak Republic
Spain
Sweden
Switzerland
Republic of Türkiye
United Kingdom
United States

The European Commission also participates in the work of the IEA

**IEA Accession countries:**

Brazil
Chile
Colombia
Costa Rica
Israel
Romania

**IEA Association countries:**

Argentina
China
Egypt
India
Indonesia
Kenya
Morocco
Nigeria
Senegal
Singapore
South Africa
Thailand
Ukraine
Viet Nam

This publication, as well as any data and map included herein, are without prejudice to the status of or sovereignty over any territory, to the delimitation of international frontiers and boundaries and to the name of any territory, city or area.

Source: IEA.
International Energy Agency
Website: www.iea.org

# አበይት ሀሳቦች

**ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ትልቅ እና ፈጣን ዕድገት ከሚያስመዘግቡ ኢኮኖሚዎች አንዷ ስትሆን፣ ይህም እያደገ ባለው ቀጠናዊ ተፅዕኖዋ እና እያደገ በሚገኘው ዓለም አቀፋዊ እውቅናዋ ይንጸባረቃል።** ዋና ዋና የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቶች ደግሞ የሀገሪቱን የኃይል አቅርቦት ገጽታ እያጠናከሩ እና እየለወጡ ይገኛሉ። ይህ ጠንካራ የልማት ራዕይ ኢትዮጵያ በቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ መሪነት እያደገ ከመጣው ሚናዋ ጋር የሚጣጣም ነው።

እንደ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ (GERD) ያሉ ግዙፍ ምልክት የሆኑ ፕሮጀክቶች ዋና ዋና የኢንጂነሪንግ ስኬቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ በኃይል ማመንጨት አቅም፣ በኃይል ደህንነት እና በቀጠናዊ ትብብር ላይ የተደረጉ ትልልቅ የዕድገት እርምጃዎችም ጭምር ናቸው። ኢትዮጵያ ሁለተኛውን የአፍሪካ የአየር ንብረት ጉባኤ በ 2025 ያስተናገደች ሲሆን፣ በ 2027 ደግሞ 32ኛውን የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ኮንፈረንስ (COP32) የምታስተናግድ ይሆናል፤ ይህም ዓለም አቀፋዊ ውይይቱ ግቦችን ከመቅረጽ ወደ ተግባራዊ ትግበራ—ትላልቅ የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነት እና ኢንቨስትመንትን ጨምሮ—በሚሸጋገርበት ወቅት ሀገሪቱን የዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ድርድሮች ማዕከል ያደርጋታል።

**የኢትዮጵያን የኃይል አጀንዳ ለማስቀጠል ጠንካራ ተቋማት፣ የተሻለ ቅንጅት እና የበለጠ አስተማማኝ ውሂብ ወሳኝ ናቸው።** የኃይል ፖሊሲ አብዛኛውን ጊዜ በትራንስፖርት፣ በኢንዱስትሪ፣ በግብርና እና በሌሎች መስኮች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ፣ መበታተንን ለማስቀረት እና የመንግሥትን ግቦች ትግበራ ለመደገፍ የፖሊሲዎች ተጣጣሚነት ወሳኝ ነው። በውኃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር (MoWE) የሚመራ የተለየ በሚኒስቴሮች መካከል የሚደረግ የቅንጅት መድረክ ቅድመ-ሁኔታዎችን ለማስማማት እና የኃይል ጉዳዮች በተያያዥ ዘርፎች ውስጥ በስርዓት የተካተቱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል። ቁጥጥር፣ ደረጃዎች እና ፍቃድ የመስጠት ኃላፊነቶች በተለያዩ ተቋማት የተበታተኑ ሲሆን፣ ግልጽ ያልሆኑ ሚናዎች ለኢንቨስተሮች እና ለገበያ ተሳታፊዎች ሂደቶችን ያወሳስባሉ። የሚኒስቴሮች፣ የተቆጣጣሪዎች እና የሕዝብ ተቋማትን የሥራ ኃላፊነት በግልጽ ማስቀመጥ እና መደበኛ ማድረግ ድግግሞሽን ይቀንሳል፣ ተጠያቂነትን ያጠናክራል፣ እንዲሁም ውሳኔ አሰጣጥን ያሻሽላል። በርካታ ተቋማት የኃይል ውሂቦችን የሚያጠናቅሩ ቢሆንም፣ አጠቃላይ ስርዓቱ አሁንም የተበታተነ ነው። ይህም በተለይም በፍላጎት በኩል ባሉ ውሂቦች እና በበቂ ሁኔታ ባልተሸፈኑ ነገር ግን ወሳኝ በሆኑ እንደ የባዮማስ አጠቃቀም፣ ከዋናው መስመር ውጭ ባሉ ስርዓቶች እና በትንሽ መጠን ማመንጨት ባሉ መስኮች ላይ የብሔራዊ የኃይል ስታቲስቲክስ ወጥነትን ያዳክማል። ነባር የቤተሰብ እና የኢንተርፕራይዝ ጥናቶችን በመጠቀም በፍላጎት በኩል ያለውን የውሂብ አሰባሰብ ማጠናከር፣ ከግልጽ የኃይል መረጃ የማተም ብሔራዊ ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ ሲሄድ፣ ግልጽነትን፣ የፖሊሲ ክትትልን እና በእውነታ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥን ያሻሽላል።

IEA. CC BY 4.0.

**የኢትዮጵያ የኃይል ዘርፍ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገት በይበልጥ ወሳኝ እየሆነ መጥቷል።** የኃይል ማመንጨት አቅም ባለፉት ዓመታት በፍጥነት ያደገ ሲሆን፣ ይህም የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን፣ ንጹህ የምግብ ማብሰያ ዘዴዎችን፣ ትራንስፖርትን እና የኢንዱስትሪ ልማትን የሚሸፍኑ ሰፋ ያሉ ስልቶችን ለማስፈጸም ያስቻለ ነው። እየሰፋ የመጣው የኤሌክትሪክ ማመንጨት አቅም እያደገ ለሚሄደው ኢኮኖሚ አስተማማኝ፣ ተመጣጣኝ እና ውጤታማ አገልግሎት መስጠቱን ለማረጋገጥ ጠንካራ እና የተቀናጀ የኃይል ስርዓት ዕቅድ ማዕቀፍ ወሳኝ ነው። ከፍተኛ የኃይል ማስተላለፊያ ብክነት እና ዝቅተኛ የስርዓቱ አስተማማኝነት የኃይል አቅራቢዎችን ገቢ የሚቀንሱ ሲሆን፣ የኢንቨስትመንት አቅምን እና ብሔራዊ ዕቅዶች ትግበራን ወደኋላ መንተታቸውን ቀጥለዋል። የውጭ ምንዛሪ እጥረት እና የውጭ ምንዛሪ ተመን መዋዠቅ ደግሞ ለኃይል መስመር ዝርጋታ፣ ለጥገና እና ለአዳዲስ ማመንጫ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ ከባህር ማዶ የገቡ ቁሳቁሶች፣ መለዋወጫዎች እና ቴክኖሎጂዎች ዋጋ እና አቅርቦት ላይ አለመረጋጋት በመፍጠር የስርዓቱን ዕቅድ የበለጠ ያወሳስቡታል።

**የኢትዮጵያ የኃይል ደህንነት የተመሰረተው የኃይል ምንጮቿ ብዝሃነትን በማረጋገጥ፣ ቀጠናዊ ትብብርን በማጠናከር እና እያደገ ለመጣው ፍላጎት የምትሰጠውን ምላሽ በማስፋት ላይ ነው።** በፈጣን እድገት ላይ ባለው ኢኮኖሚ እና እስከ 2050 225 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ከሚገመተው ሕዝብ ጋር ተያይዞ፣ የኃይል ፍላጎት በተለይም በሕንፃዎች እና በትራንስፖርት ዘርፍ በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል ተብሎ ይጠበቃል፤ ይህም አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የኃይል አቅርቦትን ከምንጊዜውም በላይ ወሳኝ ያደርገዋል። ባህላዊ የባዮማስ አጠቃቀም አሁንም አጠቃላይ የኃይል አቅርቦቱን የሚቆጣጠር ሲሆን፣ በገቡ የነዳጅ ምርቶች ላይ ጥገኛ መሆን የነዳጅ ማስገባት ስጋቶችን ይፈጥራል፤ እንዲሁም በውኃ ኃይል ወይም ሃይድሮ ኤሌክትሪክ ላይ የተደገፈ የኤሌክትሪክ ስርዓት ሀገሪቱን ለውኃ እጥረት እና ለአየር ንብረት ስጋቶች ያጋልጣታል። የፀሐይ፣ የነፋስ እና የጂኦተርማል (የምድር ውስጥ ሙቀት) ኃይል ልማትን ማፋጠን፣ ጎን ለጎንም የሀገር ውስጥ የተፈጥሮ ጋዝን በጥንቃቄ መጠቀምን መመርመር የበለጠ የተመጣጠነ እና ተቋቋሚ ስርዓት ለመገንባት ይረዳል። ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ የኃይል ቋት (Eastern Africa Power Pool) በኩል ጨምሮ በቀጠናዊ የኤሌክትሪክ ንግድ ላይ እያደገ የመጣው ሚና፣ ተለዋዋጭነትን እና አስተማማኝነትን ለማሻሻል፣ የኤክስፖርት ገቢን ለመጨመር እና የቀጠናው የኃይል ማዕከልነቷን ለማጠናከር ዕድል ይሰጣል።

**ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ በኤሌክትሪክ ተደራሽነት ረገድ ከፍተኛ እድገቶችን አስመዝግባለች።** በ2000ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ 12% ገደማ የነበረው ብሔራዊ የኤሌክትሪክ ተደራሽነት መጠን በ2024 ወደ 35% ገደማ አድጓል። ይህ እድገት ከ 2015 በኋላ ፖሊሲው ዋናውን የመስመር ዝርጋታን ብቻ ከማስፋፋት ይልቅ የመጨረሻው ማይል ግንኙነቶችን እና ጠንካራ የሆኑ የመስመር ላይ እና ከዋናው መስመር ውጭ መፍትሔዎችን ወደ ማጣመር በመሸጋገሩ የተፋጠነ ነው። እነዚህ ስኬቶች ቢመዘገቡም፣ በዓለም አቀፍ የኃይል ኤጀንሲ (IEA) መሠረታዊ የአገልግሎት ብያኔ መሠረት አሁንም 85 ሚሊዮን ያህል የሀገሪቱ ሕዝብ የኤሌክትሪክ ተደራሽነት የለውም፤ እንዲሁም ተደራሽነቱ በከፍተኛ ሁኔታ ያልተመጣጠነ በመሆኑ የከተማ ተደራሽነት ከገጠሩ አካባቢ በእጅጉ የተራራቀ ነው። ኢትዮጵያ አሁን በብሔራዊ የኃይል ስምምነት (National Energy Compact) መሠረት በ 2030 የ 75% ተደራሽነት መጠን ላይ ለመድረስ፣ እንዲሁም በብሔራዊ የኤሌክትሪክ ተደራሽነት ፕሮግራም 3.0 (NEP 3.0) መሠረት በ 2035 ሁለንተናዊ/ሁሉን አቀፍ ተደራሽነትን ለማስመዝገብ አቅዳለች። ዋናው ፈተና ተደራሽነቱ አስተማማኝ፣ ተመጣጣኝ እና ከፍተኛ የኤሌክትሪክ አጠቃቀምን የሚደግፍ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። የኤሌክትሪክ መስመር አስተማማኝነት እና የአገልግሎት ጥራት አሁንም ደካማ በመሆናቸው የቤተሰብ ፍጆታን፣ ምርታማ አጠቃቀምን እና ሰፊውን ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚገታ ሲሆን፣ ቅድመ ክፍያ የመስመር ዝርጋታ ወጪዎች ደግሞ መስመሩ በአቅራቢያቸው በሚገኝበት ቦታ እንኳ በርካታ ቤተሰቦች እንዳይገናኙ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል። ሚኒ-ግሪዶችን እና የፀሐይ ወይም ሶላር የቤት ውስጥ

I EA. CC BY 4.0.

ስርዓቶችን ጨምሮ ከዋናው መስመር ውጭ ያሉ መፍትሔዎች ራቅ ያሉ ማህበረሰቦችን ለማድረስ ወሳኝ የሚሆኑ ቢሆንም፣ በስፋት ማደጋቸው በተመጣጣኝነት፣ በፋይናንስ እና በተቆጣጣሪ ህጎች/ደንቦች ፈተናዎች የተገደበ ነው። ስለሆነም፣ የኢትዮጵያን የኤሌክትሪክ ተደራሽነት ግቦች ማሳካት አዳዲስ ግንኙነቶችን ማብዛት ብቻ ሳይሆን፣ የታለመ የመስመር ዝርጋታ ዘመናዊነትን፣ ጠንካራ የተመጣጣኝነት እርምጃዎችን እና አቅም ላላቸው ከዋናው መስመር ውጭ ያሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ሞዴሎች ከፍተኛ ድጋፍ ማድረግን ይጠይቃል።

**የኢትዮጵያ የኃይል ስርዓት ቀደሞውኑ በታዳሽ የኃይል ምንጮች በጥብቅ የተቀረፀ ነው።** በ2024 ታዳሽ ኃይል ከአጠቃላይ የኃይል አቅርቦቱ 90% ገደማ የሚሸፍን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 86% የሚሆነው ባዮኤነርጂ ነበረ። ታዳሽ የኃይል ምንጮች ለብሔራዊ የኃይል መስመሩ ሙሉ በሙሉ የሚያስፈልገውን ኤሌክትሪክ አቅርበዋል። የውኃ ኃይል የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን (GERD) ጨምሮ የኃይል ስርዓቱ ዋና ማዕከል/መሰረት ሆኖ የቀጠለ ሲሆን፣ ይህም የማመንጨት አቅምን በከፍተኛ ሁኔታ ያሳደገ እና ኢትዮጵያ በቀጠናዊ የኤሌክትሪክ አቅራቢነት ያላትን ቦታ ያጠናከረ ነው። ኢትዮጵያ ከፍተኛ ጥራት ካላቸው የፀሐይ እና የነፋስ ሀብቶች፣ እንዲሁም ገና ያልተጠቀመችበት ሰፊ የምድር ውስጥ ሙቀት (ጂኦተርማል) አቅም ትጠቀማለች፤ ይህም የኤሌክትሪክ ምንጮችን ለማብዛት፣ በውኃ ኃይል ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ እና ዘላቂነትን/ተቋቋሚነትን ለማጠናከር ይረዳል። የምድር ውስጥ ሙቀት ኃይል አስተማማኝ እና ተቆጣጣሪነት ያለው ታዳሽ ኃይልን ሊያቀርብ የሚችል ሲሆን፣ የፀሐይ እና የነፋስ ኃይል ደግሞ በውኃ ኃይል ምርት ላይ የሚታዩትን ወቅታዊ መዋዠቆች ሊያሟሉ ይችላሉ። ሆኖም፣ በእነዚህ ቴክኖሎጂዎች ላይ የተደረገው ትግበራ ከፋይናንስ፣ የመሠረተ ልማት፣ የተቋማት ቅንጅት፣ የውጭ ምንዛሪ ገደቦች እና የፕሮጀክት አፈጻጸም ጋር በተያያዙ ተግዳሮቶች ምክንያት ከታቀደው በላይ በዝግታ የተጓዘ ነው። ኢትዮጵያ የኃይል ደህንነትን ለማጠናከር እና የመንገድ ትራንስፖርትና የኢቪዬሽን ዘርፎችን ከካርቦን ነፃ ለማድረግ ከሚደረገው ሰፊ ስልት አካል አድርጋ የሀገር ውስጥ ባዮፍዩልን ማልማትንም እየመረመረች ይገኛል። ታዳሽ ቴክኖሎጂዎችን በግብርና እና በኢንዱስትሪ ለምርታማ ተግባራት ማስፋፋት—የፀሐይ መስኖን፣ አግሪቮልታይክስን እና የምድር ውስጥ ሙቀትን በቀጥታ መጠቀምን ጨምሮ—ምርታማነትን ሊያሻሽል፣ በናፍጣ ላይ ያለውን ጥገኝነት ሊቀንስ እና የገጠር ልማትን ሊደግፍ ይችላል።

**ኢትዮጵያ ንጹህ የምግብ ማብሰያ ዘዴዎችን ተደራሽ በማድረግ ረገድ አመርቂ ለውጦችን አስመዝግባለች።** በ2000ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ 2.5% የሚሆኑት የከተማ ነዋሪዎች ብቻ ንጹህ የምግብ ማብሰያ ዘዴዎችን ይጠቀሙ የነበረ ሲሆን፣ አሁን ግን ዘመናዊ የምግብ ማብሰያ መፍትሔዎች ተደራሽ የሆኑላቸው ሰዎች ቁጥር በ 9 ሚሊዮን ብልጫ አሳይቷል። ሆኖም፣ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት በነጠላ ቁጥር የተመዘገበው ጭማሪ ቢኖርም አጠቃላይ የተደራሽነት መጠኑ አነስተኛ መሻሻል ብቻ እንዲያሳይ አድርጎታል። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ካሉ አነስተኛ የንጹህ ማብሰያ ተደራሽነት ካላቸው ሀገራት አንዷ ስትሆን፣ በ2024 ወደ 120 ሚሊዮን ያህል ሕዝብ አሁንም ባህላዊ የምግብ ማብሰያ ዘዴዎች ላይ ጥገኛ ሆኖ ይገኛል። ከእነዚህም ውስጥ 8% ገደማ በዋናነት በከተሞች አካባቢ ጥቅም ላይ በሚውለው ከሰል ላይ ጥገኛ ሲሆኑ፣ 92% ገደማ የሚሆኑት ደግሞ በዕንጨት ላይ ጥገኛ ናቸው። ኢትዮጵያ በ2030 እስከ 58%፣ በ2035 ደግሞ እስከ 76% የማድረስ ታላላቅ ግቦችን ያስቀመጠች ሲሆን፣ የኤሌክትሪክ ማብሰያዎች እና የላቁ ባዮማስ ምድጃዎች የአዳዲስ ተደራሽነቶችን ይሸፍናሉ ተብሎ ይጠበቃል። እነዚህን ግቦች ማሳካት ለ91 ሚሊዮን ያህል ሕዝብ ንጹህ የምግብ ማብሰያ መፍትሔዎችን ለማስፋፋት ያስችላል። የዚህ ስኬት ደግሞ የንጹህ ማብሰያ ግቦችን በኃይል ዘርፍ ዕቅድ ውስጥ በማካተት፣ በተለይም ፍላጎቶችን አስቀድሞ በመገመት እና የኃይል መስመር አስተማማኝነት ስጋቶችን በማስተዳደር ላይ የተመሰረተ ነው። በተመሳሳይ ጊዜ፣ በኢትዮጵያ ወደ ንጹህ ማብሰያ በሚደረገው ሽግግር ውስጥ ዋጋ የመክፈል አቅም/ተመጣጣኝነት ዋነኛው እንቅፋት ሆኖ ቀጥሏል። ለብዙ ቤተሰቦች የንጹህ ማብሰያ ምድጃዎች እና ቁሳቁሶች ቅድመ ክፍያ ወጪ አሁንም ከአቅም በላይ ነው። የባዮማስ እና የባዮጋዝ መፍትሔዎች ተመጣጣኝ ሊሆኑ ቢችሉም፣ የላቁ

IEA. CC BY 4.0.

ባዮማስ እና የኤሌክትሪክ ማብሰያ ዘዴዎችን በስፋት ለመጠቀም ግን የታለመ የፋይናንስ ድጋፍ፣ የደንበኞች ፋይናንሲንግ እና ጠንካራ የአቅርቦት ሰንሰለቶችን ይጠይቃል።

**እስካሁን ያሉት የኢንቨስትመንት ዘይቤዎች የታዩ ለውጦችን እና የቀሩ ፈተናዎችን ጎልተው ያሳያሉ።** በኃይል ዘርፉ የፋይናንስ አቅርቦቱ በመንግሥት ዘርፍ የተያዘ እና በኤሌክትሪክ ተደራሽነት እንዲሁም ከመስመር ጋር በተያያዙ የታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቶች ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ የልማት ፋይናንስ ተቋማት ዋናውን ሚና የተጫወቱ እና የንግድ/የኮመርሻል ፋይናንስ ግን በተለይም ከኃይል ማመንጫት ውጭ ባሉ መስኮች የተገደበ ሆኖ ቆይቷል። በንጹህ ማብሰያ ዘርፍ፣ ታሪካዊ ኢንቨስትመንት በአንጻራዊ ሁኔታ አነስተኛ እና በዋናነት በእርዳታ ገንዘብ ላይ የተደገፈ ነበረ፤ ይህም በብሔራዊ የንጹህ ማብሰያ ፍኖተ ካርታ መሠረት የወደፊት ፍላጎቶችን በጣም አነስተኛ ክፍል ብቻ የሚሸፍን ነው። ኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ገደቦችን ለማቃለል እና የባለሀብቶችን/የግል ዘርፉን ተሳትፎ (የውጭ ኢንቨስትመንትን ጨምሮ) ማዕቀፍ ለማጠናከር የተወሰዱ እርምጃዎችን ጨምሮ በማክሮ ኢኮኖሚ እና በተቆጣጣሪ ህጎች ማሻሻያ በኩል ሰፊውን የኢንቨስትመንት አካባቢ አሻሽላለች። ሆኖም፣ አሁንም ባለው ከፍተኛ የካፒታል ወጪ እንደሚታየው ለኢንቨስትመንት እንቅፋት የሆኑ ነገሮች እንደቀጠሉ ይገኛሉ። የባንክ ብድር የማግኘት አቅምን ለማሻሻል፣ የኢንቨስተሮችን ስጋት ለመቀነስ እና የቅናሽ እንዲሁም የተቀላቀለ የፋይናንስ አጠቃቀምን ለማስፋት ተጨማሪ ማሻሻያዎች አስፈላጊ ሆነው ይቀጥላሉ።

IEA. CC BY 4.0.

# የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦች ለኢትዮጵያ

## አጠቃላይ የኃይል ፖሊሲ

1. የኢትዮጵያን የኃይል ዘርፍ ውጤታማ ልማት ለማስፋፋት እና የኃይል ጉዳዮችንና ቅድመ-ሁኔታዎችን በሁሉም ዘርፎች ውስጥ አካታችነትን ለማረጋገጥ በሚኒስቴሮች ውስጥ፣ በሚኒስቴሮች መካከል እና በዘርፎች መካከል ያለውን ቅንጅት ማጠናከር።

2. ለኢንቨስተሮች ግልጽነትን እና ተገማችነትን ለማሻሻል የእያንዳንዱን ሚኒስቴር እና የመንግሥት ተቋም ተቋማዊ ኃላፊነቶች፣ ሚናዎች እና ተጠያቂነቶች በግልጽ ማስቀመጥ።

3. የኃይል መረጃዎችን ክትትል፣ ቁጥጥር እና ሪፖርት ማድረግን ለማሻሻል የመረጃ ስብስብ ስርዓትን ማበጀት/በስርዓት መምራት።

4. በኃይል ዘርፍ ያለውን እድገት ለማፋጠን እና ኢንቨስትመንትን ለመሳብ COP32ን የማስተናገድ ዕድልን/ተነሳሽነትን በአግባቡ መጠቀም።

## የኃይል ዘርፍ

5. ለገበያ ተሳታፊዎች እና ለኢንቨስተሮች ስለ ገበያው መዋቅር ያለውን ግልጽነት እና ተገማችነት ማሻሻል።
6. በልዩ ልዩ የተከፋፈለ የኃይል ማመንጨት እና በቀጠናዊ የኃይል ንግድ በኩል የኃይል ደህንነትን እና ዘላቂነትን ማጠናከር።
7. ውጤታማነትን እና አስተማማኝነትን ለማሻሻል እንዲሁም የሀገሪቱን እያደገ የመጣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፍላጎቶች ለማሟላት የተቀናጀ የኃይል ስርዓት ዕቅድን ማጠናከር።
8. የግል ካፒታል/ኢንቨስትመንት ፍሰትን ለማፋጠን አጠቃላይ የኃይል ንግድ አካባቢውን የበለጠ ማሻሻል።

## ታዳሽ የኃይል ምንጮች

9. እርስ በእርስ የሚደጋገፍ በታዳሽ ኃይል ላይ የተመሰረተ የኃይል ስርዓት መቅረጽ።

10. በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለኃይል እና ለሙቀት አገልግሎት የሚውሉ የታዳሽ የኃይል ቴክኖሎጂዎች ትግበራ እና አጠቃቀምን ማፋጠን።

11. የኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ባዮኤታኖል እና ባዮዲዜል (ተፈጥሯዊ ናፍጣ) ምርት የረጅም ጊዜ ዘላቂነትን ማረጋገጥ።

12. በጥሩ ሁኔታ የተዋቀረ፣ ግልጽ እና ተወዳዳሪ የጨረታ ስርዓት መቅረጽ እና መተግበር።

IEA. CC BY 4.0.

## የኤሌክትሪክ ተደራሽነት

13. እያደገ የሚሄድ የፍላጎት ጭማሪን፣ ጠንካራ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፋይናንስን እና ዘላቂ የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን ለማስመዝገብ ከፍተኛ አቅም ባላቸው አካባቢዎች የታለሙ የመስመር ማሻሻያዎችን በማድረግ አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አገልግሎቶችን ማስቀደም።

14. ከመስመር ጋር የተያያዙ እና ከዋናው መስመር ውጭ ያሉ የኤሌክትሪክ ተደራሽነት ግቦችን ማሳካትን ለመደገፍ የተመጣጣኝነት/የዋጋ እንቅፋቶችን መፍታት።

15. በግልጽ የተቀናጀ ጂኦስፓሻል ዕቅድ፣ በተቀነሰ የተቆጣጣሪ ህጎች እርግጠኛ ያለመሆን ሁኔታ እና በተለዩ የገበያ ማመቻቸቶች በኩል የግል የሚኒ-ግሪድ ኢንቨስትመንትን ማሳለጥ።

## የንጹህ ማብሰያ ተደራሽነት

16. የመስመር ዝርጋታ ዘመናዊነትን እና ማስፋፋትን ከቤተሰቦች የንጹህ ማብሰያ መፍትሔዎችን የመቀበል እና የመግዛት አቅም ጋር የሚያጣጥም፣ ከብሔራዊ የኤሌክትሪክ ተደራሽነት ፕሮግራም ጋር የተጣጣመ አጠቃላይ የንጹህ ማብሰያ ፍኖተ ካርታ የትግበራ ዕቅድ ማዘጋጀት።

17. የንጹህ ማብሰያ ፍኖተ ካርታ የተደራሽነት መጠን ግቦችን ለማሳካት እንዲረዳ የንጹህ ማብሰያ መፍትሔዎችን ስብጥር ማስፋት እና ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን ምድጃዎች ማስቀደም።

18. ለሽግግሩ የሚያስፈልገውን ኢንቨስትመንት የሚስብ፣ የሀገር ውስጥ የገበያ ተሳታፊዎችን የሚያጠናክር እና የቤተሰቦችን አጠቃቀም የሚያፋጥን ምቹ ሁኔታን ለንጹህ ማብሰያ ዘርፍ መፍጠር።

IEA. CC BY 4.0.

# ኢትዮጵያ 2026

## የኢነርጂ ፖሊሲ ግምገማ

ኢትዮጵያ እያደገ በሚገኘው ቀጠናዊ ተፅዕኖዋ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ እየጎላ በሚመጣው ህልውናዋ ከአፍሪካ ትልልቅ እና ፈጣን ዕድገት ከሚያስመዘግቡ ኢኮኖሚዎች አንዷ ናት። ሀገሪቱ የኃይል አቅርቦት ገጽታዋን እየለወጡ ባሉ ዋና ዋና የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቶች የተደገፈ ታላቅ የልማት ራዕይ አስቀምጣለች። እንደ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያሉ ግዙፍ ምልክት የሆኑ ፕሮጀክቶች የኃይል ማመንጨት አቅምን በከፍተኛ ሁኔታ ያሳደጉ፣ የኃይል ደህንነትን ያጠናከሩ እና ኢትዮጵያ በቀጠናዊ የኤሌክትሪክ ንግድ ውስጥ ያላትን ሚና ያጎሉ ናቸው።

የኢትዮጵያ በዋናነት በታዳሽ ኃይል ላይ የተመሰረተ የኃይል ስርዓት፣ በኃይል ማመንጨት አቅም ላይ የተደረጉ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶች እና በኃይል ዘርፍ የተከናወኑ ሰፊ ማሻሻያዎች እያደገ የመጣውን የኃይል ፍላጎት ለማሟላት ጠንካራ መሠረት ይጥላሉ። የኃይል ዘርፉ የኢትዮጵያን የልማት ምኞቶች ለማስቀጠል እና ቀጠናዊ መሪነቷን ለማጠናከር ማዕከላዊ ሚና ይጫወታል።

ይህ የኢትዮጵያ የኃይል ፖሊሲ ግምገማ (Energy Policy Review of Ethiopia) በኢትዮጵያ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የኃይል ኤጀንሲ (IEA) መካከል ባለው እያደገ የመጣ አጋርነት ላይ በመመስረት እና ኢትዮጵያ በ 2027 COP32ን ለማስተናገድ በምትዘጋጅበት ወቅት በጋራ የተዘጋጀ ነው።

በአዲስ አበባ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ከተካሄደው ጥልቅ የግምገማ ተልዕኮ በኋላ፣ ይህ ሪፖርት የሀገሪቱን የኃይል ፖሊሲዎች፣ የታዩ ለውጦችን እና የቀሩ ፈተናዎችን ይገመግማል። ሪፖርቱ አፈጻጸምን ለማጠናከር፣ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ፣ የኤሌክትሪክ እና የንጹህ ማብሰያ ተደራሽነትን ለማስፋፋት፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ዘላቂ፣ ተመጣጣኝ እና ሁሉን አቀፍ ወደሆነ የኃይል ሽግግር ለማድረግ የምታደርገውን ጥረት የሚደግፉ የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ያቀርባል።